(ለጀነት ነዋሪዎች) አንድ ተጣሪ ይጣራና "ለናንተ ጤና አላችሁ መቼም አትታመሙም፤ ለናንተ ህይወት አላችሁ መቼም አትሞቱም፤ ለናንተ ወጣትነት አላችሁ መቼም አታረጁም፤ ለናንተ በፀጋ ውስጥ መጣቀም አላችሁ መቼም አትቸገሩም።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይና ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ
(ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: «(ለጀነት ነዋሪዎች) አንድ ተጣሪ
ይጣራና "ለናንተ ጤና አላችሁ መቼም አትታመሙም፤ ለናንተ ህይወት አላችሁ መቼም አትሞቱም፤ ለናንተ ወጣትነት አላችሁ መቼም
አታረጁም፤ ለናንተ በፀጋ ውስጥ መጣቀም አላችሁ መቼም አትቸገሩም።" ይህም ይህ የአላህ ዐዘ ወጀል ንግግር ነው: {ይህች ጀነት
ትሰሩት በነበራችሁት ተሰጣችኋት በማለት ይጠራሉ።} [አልአዕራፍ: 43]»
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የጀነት ነዋሪዎች በጀነት ውስጥ እየተጣቀሙ ሳሉ አንድ ተጣሪ እንዲህ በማለት እንደሚጣራ አወሱ "ጀነት ውስጥ ለናንተ ጤና አላችሁ መቼም ትንሽ እንኳ ብትሆን ህመም አትታመሙም። ለናንተ ህያውነት አላችሁ፤ ትንሿ ሞት የሆነችውን እንቅልፍ እንኳ ቢሆን መቼም ጀነት ውስጥ አትሞቱም። ለናንተ ወጣትነት አላችሁ፤ መቼም ጀነት ውስጥ አታረጁም። ለናንተ ጀነት ውስጥ መጣቀም አላችሁ፤ መቼም ጀነት ውስጥ አታዝኑምም አትቸገሩምም። ይህም ይህ የአላህ ዐዘ ወጀል ንግግር ነው: {ይህች ጀነት ትሰሩት በነበራችሁት ተሰጣችኋት በማለት ይጠራሉ።} [አልአዕራፍ: 43]

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/8341